January 3,2005

# ዝክሩ ለሳሙኤል፤

(ሙሉቀን)

አንቺ ሀገር ኢትዮጵያ - መልእክተኞች መጠናል፥
አንተ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ - መልእክት አለን ስማን፥
ግፉአን ጎስቋላ ተራ የሕዝብ ልጆች - ሁሉም ይስሙን!
በእምቢልታ በበገና ይነገር - እነሆ መልእክታችን አዋጅ!
የሕዝብና የሀገር ሃብት ጠፍቷል - የቃል ኪዳኑ ግምብ አካል ፈርሷል።

ንባቤ ቃሉ ከጀግናህ (ከሳሙኤል አለማየሁ) - እነሆ እንዲህ ይላል፥ እንዲህ ልኳል፥
'በዚያን ጊዜ ጨለማ ውስጥ እንቅልፍ ላይ - ህልው ሆኖ የአገሬ ምድር፥
ሲላወስ ሲፈራገጥ ጣረሞቱን - አየሁት መለመላ ራቁቱን፥
በመሃሉ እንጉርጉሮ ዋይታ - የአረጋውያን ኡኡታ የህጻናቱ ሽልብታ፥
የእህት እናቶች እምባ - የጥቂቶች መለኮታዊ ቀረቤታ፥
የህዳጣን ብሄረሰቦች እመቃ - የሌሎችም እንግልት ሰቆቃ፥
የገበሬውና ሠርቶ አደሩ አቤቱታ - የአደባባይ ላይ ሃብት ንብረቱ ዝርፊያ፥
በረሃብና ጥም ላይ ዳንስ ሁካታ - የሚረገጡት ብዙሃን ጫጫታ
በህልሜ ...
ኢትዮጵያ ታየችኝ ገዝፋ - ይህን ሁሉ ይዛ፤
ታሥራ ተደይና አቅም አጣ ።

በምጽአቱ ሕዝብ ሲያለቅስ - ብሶት እንጉርጉሮውን ሰምቼ
በደነገጠ ሥነ-ልቦናዬ - በሰመመን አቅንቼ፥
መንፈሰ ሥራ 'እኔን' እየመረመርኩ ቁሜ - የሰማሁትን ያየሁትን ባይኔ፤
ከዚያም ...
በጨለማው ውስጥ አይኔን ገልጬ - ጓደኞቼን አማክሬ ተማክሬ
የሰማሁ ያየሁትን አስረድቼ - ከእነሱም ያስተዋሉትን የሚያውቁትን ጠይቄ፤
መክረን ዘክረን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ - አዳምጠን የብዙሃኑን አባዜ
አምነን ተቀብለን ቃሉን - አብዛኞቻችን - እሷም፥ እሱና እኔ።

ከዚህም ከዚያም በላይ በበኩሌ - ፀንቼ ቀጥዬ ለዘመናት ዘምሬ፥
ረጅሙን መንገድ ተጉዤ - ተራራውን ወጥቼ ፥ ቁልቁለቱን ወርጄ
ብዙውን እንቅፋት አልፌ ገደሉን ተሻግሬ- ለሚከተሉኝ ሁሉ ምልክቱን ትቼ፥
የሚወዱኝን ወድጄ የሚጠሉኝን አስተምሬ - ታግዬ ለጊዜዬ ትውልዴን ወክዬ፥
ሕይወቴን ሙሉ ለሕዝቤ ለሀገሬ - ለነገ ወዲያ ብሩህ ዓለም አልሜ፥
ሰለቼኝ ደከመኝ ሳልል የቻልኩትን ሁሉ ጥሬ - አርፌያለሁ ተጠናቀቀ ሩጫዬ፤
በአካል በሥጋ ደህና ሁኑ - ተፋቅራችሁ በእምነት ቀጥሉ፥
በዓላማ ህብረት ተሳሰሩ ፥ ጽኑ ...
ትላለች ነፍሱ የአንበሳው - የጓድ ሳሙኤል አለማየሁ።

ጓዶቹ - እኛስ ምን እንበል?
ጀግና ሲሸኝ ሲሰናበት - ታጋይና አታጋይ በአካል ሲለይ፥

ለእናት ሀገር ኢትዮጵያ - ለሕዝባችን ምን እንመስክር?
ኮለል ባለ አጭር ቃል ... ለአንድ አፍታ÷
ሐውልቱ ኢሕአፓ - ከብሮ የሚያስከብር ጀግና አጣ፤
ኢትዮጵያ ከል ትልበስ - ሕዝቧም እርሙን ያውጣ÷
ይረዳው ይወቀው - ማን እንደነበር ይህ ጀግና÷
ለጠባቦች እሬት  - ለትምክህተኞች ሳማ÷
ለአምባገነኖች የማይተኛ - ለሸረኞች የከፋ
ፍትህና ርትእ÷ እኩልነት አምላኪ - የአንድነት ዕድገት ተስፋ
ይህ ነበር ሳሙኤል - አባ ጥበብ የእኛ አንበሳ::

ጓድ ሳሙኤል! - የኢሕአፓ ውስጠ ልብ በላይ÷
በዘዴ ቢሆን ኖሮ በትግል - ትለጋው ነበር ሞትን÷
ትስቅበት ነበር መውደቅን - ተቸንፎ መተኛትን፤

ጻሩ ህግ ሆነና የተፈጥሮ - ስልጣኑ ሆኖ የሞት÷
ተራ በተራ መርጦ ሊወስድ - ያለይግባኝ ተደንግጎለት÷
ስትባክን ድንገት ቢያገኝህ - መብቱን አክብረህ ወደቅህለት::

ጓድ ሳሙኤል! ...
ቆርጠህ ከተለየህ - እንግዲህ እናስታውስህ÷
ከቆራጥነትህ ባሻገር - ከገቢራዊ እልፍ ፅናትህ÷
የምንወድህ የምናከብርህ - እንዲህ ነበር ያንተ ፀባይ:-
ከማስመሰል የጸዳ ፍቅር - በመስጠት የሚሻት ክብር÷
ያልተድበሰበሰ ግልጽ አቋም - ከብረት የጠነከረ ባህሬ-ሥርዓት÷
ነበር ያንተ ሃብተ-ባህርይ  በረከት -
          ወርሰን የምናስተላልፈው ዘላለማዊ ህይወት::

ዝክሩ ለሳሙኤል
የሰማእታት ነፍስ ይማር÷
አሜን!